ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)
የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች

# የጫት መዘዝ በኢትዮጵያ፡- ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖውና የችግሩ ፈቺ የፖሊሲ አቅጣጫዎች

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው::

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ኃብዞ ያወያያል::

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል::

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን::

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

ኢትዮጵያን ከምትገኝበት የድህነትና የኋላቀርነት አረንቋ የጣሏት በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ህብረተሰባዊ ሁኔታዎች እንዳሉ ይታወቃል። ከዚህም አረንቋ ለመውጣት የምታደርገውን ጥረት የሚፈታተኑ ጥቂት የማይባሉ ነባር ተግዳሮቶች መኖራቸው እሙን ነው። የነዚህ የቆዩ የዕድገት ማነቆዎች መኖር ሳያንስ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብቅ ያሉ ወይም መልካቸውን እየቀያየሩና እየተስፋፉ የመጡ ተደራራቢና ተጋጋዥ አሉታዊ ህብረተሰባዊ ክስተቶች የሃገሪቱን ቀጣይ ደህንነትና የወደፊት እርምጃ አሳሳቢ አድርገዋቸዋል። ከነዚህም ውስጥ ወደ ወረርሺኝ ደረጃ የተሸጋገሩት ቅጥ-ያጡ የአልኮል፣ ትምባሆ፣ ሺሻ፣ ጫት፣ ፓርኖግራፊ አዘውትሮ ተጠቃሚነት ተጠቃሽ ናቸው። ሁኔታው እንደዚህ በአሳሳቢ ደረጃ እያለ ግን፣ በነዚህ የኋለኞቹ አሉታዊ ክስተቶች ላይ በቂ ጥናትና ውይይት ሳይደረግባቸው ቆይቷል። መንግሥትም ተገቢና ዘላቂ የሆኑ የመፍትሄ እርምጃዎችን ለመውሰድ መሠረት የሚሆኑ ወጥ ፖሊሲዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ከማዘጋጀትና ከማወጅ በመታቀብ ጉዳዩን በቸልተኝነት ያዝ-ለቀቅ ሲያደርግ ይታያል። በመሆኑም፣ ሁኔታው በዚህ የፖሊሲ ፍሬ-ሃሳብ ፅሁፍ በአጭሩ የተዘገበውን ሰፊ ጥናትና መሰል ጥረቶችን ጋብዟል። የጥናቱ ውጤት ከሌሎች መሰሎቹ ጋር ተዳምሮና በውይይት ዳብሮ መረቀቅ ላለባቸው የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎች ግብአት እንደሚያበረክት ይታመናል።

## 1. የጥናቱ ዳራ

ጫትን በተመለከተ የተሰበሰቡ ተጨባጭ መረጃዎች እና የሕዝብ አስተያየት የሚስማሙበት አንድ መደምደሚያ አለ። ይኸውም፣ አሁን በምንገኝበት የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ መላ ኢትዮጵያን እያጥለቀለቀ ያለ ማዕበል ተከስቷል። ይኸም፣ በሰፊው የሃገሪቱን የእርሻ መሬት እና የሕዝቦቿን አዕምሮ በመውረር ላይ የሚገኘው ጫት (አንዳንዴ ደግሞ ቃት፣ ጋድ፣ ካት፣ ሚራ ወዘተ... ) በመባል የሚታወቀው ሱስ አሲያዥ ዕፅ ነው። ይህን ዕፅ የማብቀልና የመቃም ልምድ ቀደም ሲል በሃገሪቱ ምስራቃዊ ክፍል በተለይም በሐረርና በአካባቢዋ ዘመናት ያስቆጠረ ቢሆንም ወደ ሌሎቹ ፈፅሞ ይታወቅባቸው ወደ አልነበረው የሃገሪቱ አካባቢዎች በስፋት የተዛመተው ከ1960ዎቹ ወዲህ እና በተለይም ባለፉት ሁለት አሠርተ-ዓመታት መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በአሁኑ ሰዓት ጫት የሚመረትበት መሬት በአመት የ160 በመቶ ዕድገት እያስመዘገበ ሲሆን፣ በአመት የሚመረተው ጫት መጠንም በለፉት አምስት አመታት የ243 በመቶ ዕድገት አሳይቶ ይገኛል። በ2003 ዓ.ም. ከሃገሪቱ የገጠር ነዋሪ ቤተሰብ ውስጥ አንድ-አምስተኛ የሚሆኑት ይነስም ይብዛ የተወሰነ የጫት ተክል ያላቸው መሆኑ፣ የጫት ምርት ምን ያክል የገበሬውን ቀልብ እንደማረከና በገበሬው ሕዝብ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ሚና ያሳያል።

በተመሳሳይ፣ የጫት ግብይት በበኩሉ እጅግ ከፍተኛ ዕድገትን አስመዝግቧል። የጫት የአገር ውስጥ ዝውውር እና ንግድ የበርካታ ዜጎች መተዳደሪያ ሲሆን የውጭ ንግዱ ደግሞ በ2008/9 ዓ.ም 272.4 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ምንዛሬ ለሃገሪቱ ያስገኘ ሲሆን ከአምስት ዓመታት በኋላ በየአመቱ 58.1 በመቶ ዕድገት በማምጣት 650.8 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል ተብሎ ሁለት ዓመታትን ባስቆጠረው ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተይዞለታል።

የጫት የሃገር ውስጥ ፍጆታም ቢሆን፣ እንደዚሁ ወደ ሰማይ መጥቋል። በ2003 ዓ.ም የተካሄደ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የዳሰሳ ጥናት እንዳሳየው ከሆነ ከጠቅላላው ወንድ ሕዝብ መካከል 27.6 በመቶ እና ከጠቅላላው ሴት ሕዝብ

መካከል 11.0 በመቶ የሚሆኑት ጫት ቅመው የሚያውቁ ናቸው። ይህ አጠቃላይ ገፅታ ሲሆን በአንዳንድ ከተሞችና አካባቢዎች ደግሞ የጫት ቃሚው ሕዝብ በመቶኛ ሲሰላ ከዚህ እጅግ በጣም ከፍ ብሎ ፣ ለምሳሌ በሐረር ከወንዶቹ 81.9 በመቶ ከሴቶቹ 39.2 በመቶ ሆኖ ይገኛል። በተጨማሪ፣ በህብረተሰባችን የተስፋፋው የጫት ተጠቃሚነት ድንበር የለሽ ሆኖ ወንዶችና ሴቶችን፣ በተለያዩ የዕድሜ እና የገቢ እርከን ያሉትን፣ ገጠሬና ከተሜዎችን፣ በትምህርት የገፉና ወደ ኋላ የቀሩትን፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮችን ወዘተ... በመላ የሚመለከት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

## 2. አላማ እና የመረጃ አሰባሰብ ስልትና ዘዴ

የዚህ ጥናት አላማ ጫት እያሳደረ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለመለካት ሳይሆን፣ የጫት ቃሚነት እና ሱሰኝነት እንዴትና በምን ምክንያት እንደሚስፋፋ፣ ጫት በየትና እንዴት እንደሚዘወተር፣ ምን ምን እና በእንዴት የተለያዩ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖችን እንደሚያሳድር፣ እና ህብረተሰቡ ለዚህ በመስጠት ላይ ያለውን ምላሽ ጭምር በጥልቀት መረዳት፣ መዘገብ እና ይህንን መሰረት ያደረጉ እና ሊተገበሩ የሚችሉ የፖሊሲና የሕግ ዕርምጃዎችን አንጥሮ በማውጣት ለህዝባዊ ውይይትና ለፖሊስ እና ለሕግ-አውጭ አካላት ዘርዝሮ ማቅረብ ነው።

ዋናው የጥናቱ ስልት የጫት ዝውውርና ቃሚነት የሚመለከታቸውን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች አባላትን ለይቶ በማውጣት እነዚህን ሊወክሉ የሚችሉ ግለሰቦችን በግልና በቡድን በማነጋገር መረጃ መሰብሰብና አስተያየቶቻቸውን በራሳቸው አገላለፅና ድምፅ ማሰማት ነው። በዚህ ዓይነት፣ በአሶሳ እና በሐረር ከተሞች በተካሄዱ የመስክ የመረጃ ስብሰባ ሥራዎች አማካይነት ምልከታን የጨመሩ 20 ጥልቅ ቃለመጠይቆች ከጫት ሱሰኞች፣ ከጫት ሱስ አገጋሚዎች፣ ከጫት ተላቃቂዎች እና ከቤተሰብ አባሎቻቸው ጋር ተካሂደዋል። በተመሳሳይ፣ 15 ተጨማሪ ጥልቅ ቃለመጠይቆች ከጫት ቃሚነት ጋር ግንኙነት ካላቸው ዝሙት-ተዳዳሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ የአእምሮ ህክምና ባለሙያዎች እና የፌደራሉ መንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ተካሂደዋል። 19 ቡድንተኮር ውይይቶችን እና የቡድን ቃለመጠይቆችን፣ ከሃይማኖት እና ማኅበረሰብ መሪዎች፣ ከዩኒቨርሲቲ አመራሮችና ከተማሪ ተወካዮች፣ ከክልላዊ መንግሥት ቢሮዎች እና ከከተሞች መስተዳደር የሥራ ሃላፊዎች ከፍትህ አካላት እና ከፖሊስ ኦፊሰሮች እንዲሁም ከሲቪል ማኅበረሰብና የማኅበረሰብ ድርጅቶች ወኪሎች ጋር አካሂዷል። ከተለያዩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች ተጨማሪ የፅሁፍ መረጃ ሰብስቧል። በተመሳሳይ፣ በጫት የተለያዩ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎች እና መፍትሔዎች ላይ የተካሄዱ ሳይንሳዊና የሕክምና ጥናት ውጤቶችንም በመዳሰስ ተመልክቷል።

## 3. የጥናቱ ዋናዋና ግኝቶች

*የጫት ቃሚነትና ሱሰኝነት መስፋፋት፡-* በአሁኑ ጊዜ መላ የሃገሪቱን ክፍሎች እያጥለቀለቀ የሚገኘው የጫት ተጠቃሚነትና ሱሰኝነት መልካምድራዊ ግስጋሴው ብቻ ሳይሆን በሚዘዋወረው እና በሚቃመው ጫት መጠንና በሚጠፋው ጊዜ ጭምር እየተንሰራፋ መምጣቱን ጥናቱ ያሳያል። መልካምድራዊ ግስጋሴው ቀደም ሲል በልማዳዊ አስተሳሰብና አያያዝ ታርቆ በስራ ላይ ይውል ከነበረባቸው አካባቢዎች ወደ አዳዲስ ይዞታዎች መዛመቱን ያመለክታል። በመሆኑም፣ በቀድሞ የይዞታ ቦታዎቹ "የልማድ ዕዳ" ሲሆን በአዳዲሶቹ ይዞታዎቹ ደግሞ ልማታዊ ተቋሞችን ተከትሎ የገባ "የዘመናዊነት ዕዳ" ነው። የመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታን የትምህርት ማዕከላት ምስረታን፣ የንግድ እና የአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች መስፋፋትን፣ የመንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየተዋረዱ መበራከትን፣ ወዘተ ...በመንተራስ የጫት ተጠቃሚነት እና ሱሰኝነት ከአንድ ወገን አዳዲስ አካባቢዎችን በእጁ ሲያስገባ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በስሩ በቆዩት ነባር ይዞታዎቹ ጭምር ከበፊቱ በባሰ ደረጃ እየተስፋፋና ቅጥ እያጣ መጥቷል።

*የጫት ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ፡-* ጫት በሕብረተሰቡ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ፣ ባጠቃላይ አሉታዊ ወይም ጎጂ መሆኑ በአንክሮ ሲወሳ፣ ጥናቱ ምናልባት መረጃ ሰጭዎቹ የጫት ፋይዳዎች ናቸው የሚሏቸው ነገሮች ይኖሩ እንደሁ በማለት ያካሄደው ምርመራ ግን ከሚላ-ጎደል ውጤት አልባ ሆኖ ቀርቷል። የጫትም ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ጠንቆች እንደሚከተለው ተዘርዝረው በዋናው ፅሁፍ በሰፊው ታትተዋል።

የጫት ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ በንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍሎ በዝርዝር ቀርቧል ፣ እነሱም ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

- የቤተሰብ ኑሮ እና ኢኮኖሚ
- የሴቶች እና የልጆች ሁኔታ
- የአካባቢ ኢኮኖሚ እና የአካባቢ ማኅበረሰብ ሁኔታ
- የጤናና የጤና ጥበቃ አገልግሎት (የአካል፣ የአዕምሮ እና የስነተዋልዶ ጤና)
- የትምህርት እና የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርስቲዎች እና ሌሎች ተቋማት)
- የወንጀል እና የእርማት ሁኔታ
- የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት አሰጣጥ
- የጫት በጎ ጎኖች መኖር ወይም አለመኖር ጉዳይ፡፡

## 4. የጫትን ተጠቃሚነት እና ሱሰኝነት ለመቀልበስ እና ሱሰኞችን ለመታደግ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች

የጥናቱ አንድ ዋና ክፍል የሆነው ይህ ጉዳይ በጥልቅ ታይቷል። በአሶሳና በሐረር ከተሞች የጫትን ወረርሽኝ ለመቀልበስ አበረታች ስራዎች እየተካሄዱ መሆኑ ተረጋግጧል። በሁለቱም ከተሞች ነዋሪውን

ሕዝብ ስለ ጫት ትክክለኛ ግንዛቤ እና ተነሳሽነት እንዲኖረው የሚያደርጉ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል። እነዚህን ተግባራት በማስፈፀም ዋነኛውን ሚና በመጫወት ላይ ያሉት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሆኑ፣ የመንግሥት አካላት አስተዋፅኦ ግን በአብዛኛው ከድጋፍ ሰጭነት ያለፈ አይደለም።

ይህን በተመለከተ በአሶሳ ከተማ ከተካሄዱት ፕሮግራሞች ውስጥ አንፀባራቂ የሆነው፣ ብግዳን በተባለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት እና በአሶሳ ከተማ ሆስፒታል ትብብር በሦስት የአንድ-አንድ ወር ዙሮች የተካሄደው የጫት ሱሰኞችን በሕክምና የማላቀቅ ተግባር ነው። በሐረር ከተማ ከተካሄዱት ፕሮግራሞች መካከል መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ቀስቃሽነት 90 የሚሆኑ የሙስሊም አፎሻዎችን እና የክርስቲያን እድሮችን በማስተባበር እና በእነርሱ አማካይነት የማኅበረሰብ ውይይቶችን በማካሄድ፣ የሕዝቡ አይንና አንደበት ተከፍቶ የጫትን የመስፋፊያ መንገዶችና ጉዳቶቹን በማሳወቅ ቢያንስ መጭውን ትውልድ ከዚህ ማጥ ለማዳን በመውሰድ ላይ ያለው እርምጃ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት ፈር-ቀዳጅ የሆኑና እንደ የናሙና ሙከራ የሚቆጠሩ እንጅ በአገር ደረጃ የጫትን ወረርሺኝ ለመቀልበስ የሚችሉ አይደሉም። ሆኖም ከነዚህ ሙከራዎች ትምህርት በመቅሰም የወደፊቱን አገር-አቀፍ እርምጃ ማሰላሰል ይቻላል። በተለይ፣ የገጠሙዋቸውን ተግዳሮቶች ነቅሶ ለማውጣት በተደረገው ጥረት ተደጋግሞ በዋነኛነት የተጠቀሰው የጥረት ሣንካ የጫትን አመራረት፣ ዝውውር፣ አሻሻጥና አጠቃቀም በተመለከተ ምንም ዓይነት ወጥ መንግሥታዊ ፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ነው።

### 5. መፍትሄ፡- የጫትን ወረርሽኝ ለመግታትና ሱሰኞቹን ለመታደግ አገር-አቀፍ የፖሊሲ እና የሕግ ምላሽ መስጠት

ከመስክ ጥናቱ እና ከመዛግብት ምርምሩ ግኝቶች በመነሳት፣ ፅሁፉ ሊተገበሩ ይችላሉ ያላቸውን የመፍትሄ ሃሳቦች ዝርዝር አቅርቧል። ምንም እንኳን ጫት እያስከተለ ያለው ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚጠይቀው ምላሽ የዚህን ዕፅ ፈፅሞ መታገድ ቢሆንም፣ ይህን ለማድረግ የዕፁን መመረት፣ መዘዋወር እና መቃም ሕገ-ወጥ አድርጎ በመፈረጅ ለመዋጋት መሞከሩ ውጤት-አልባ ከመሆን አልፎ ይህ ነው የማይባል ማኅበራዊ ቀውስ ሊያስከትል መቻሉን ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ነው።ሌሎች አገሮች በአደንዛዥ ዕፆች እና በአልኮል መጠጦች ላይ የሞከሯቸው እንደዚህ ያሉ አጠቃላይ እገዳዎች እንዳሳዩት፣ የዚህ ዓይነቱ እርምጃ ለወንጀለኛ ቡድኖች መፈልፈልና መጠናከር ሰፊ ዕድል ከመፍጠር ውጭ ምንም ተጨባጭ አዎንታዊ ውጤት አላሳየም። ስለዚህ፣ ፅሁፉ የሚያቀርበው የመፍትሄ ሃሳብ በአጭሩ የሚከተለው ነው።

አሁን ያለው ልቅ የጫት አመራረት፣ ዝውውር፣ አሻሻጥ እና አጠቃቀም እንዳለ መቀጠል የለበትም። በሌላ በኩል ደግሞ ጫትን ፈፅሞ የማገድ አማራጭ በስራ ላይ ለማዋል የማይቻልና መዘዘ-ብዙ ነው። ስለዚህ፣ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሊወሰድ የሚችለው፣ የሚያስፈልገው እና የሚገባው፣ በባለሙያዎች ተረቀውና ሕዝብ መክሮባቸው በመበልፀግ በመንግሥት አዋጆች የሚፀድቁና የሚተገበሩ ፖሊሲና ሕጎችን አርቅቆ በማወጅ የጫትን አመራረት፣ ዝውውር፣ አሻሻጥ እና አጠቃቀም ሥርዓት በማስያዝ መቆጣጠርና እንዲቀንስ ማድረግ ነው።

ይህ፣ የመቆጣጠር ሥርዓት የማስያዝ አማራጭ አንዳንዶች እንደሚሉት አገሪቱ ከጫት የምታገኘውን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ አያደርገውም፤ እንዲያውም የሃገር ውስጥ ፍጆታን በመቀነስ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የጫት መጠን እንዲጨምር ያደርገው እንደሆነ እንጂ፣ በማለት ፅሁፉ ያትታል። በተጨማሪ፣ ጫትን ሥርዓት በማስያዝ መቆጣጠር፣ አንዳንዶች እንደሚሉት የሰብዓዊ መብት ረገጣ ሳይሆን፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች አባላትን ማለትም የሴቶችን፤ የልጆችን እና የሌሎች ከጫት ንክኪ ነፃ የሆኑ ሰዎችን ሰብዓዊ መብት ጭምር ለማስከበር የሚረዳ መሆኑን ፅሁፉ ያሳያል።

በተጨማሪ፣ ፅሁፉ የተለያዩ የመንግሥት አዋጆችን፣ ፖሊሲዎችን፤ ዶኩዩመንቶችን እና የጥናት ዘገባዎችን በመመርመር ጫትን በተመለከተ ያለውን የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፍ ክፍተቶችና መጣረሶችን በገሃድ ያሳያል። በመቀጠልም ጫትን ፈር ለማስያዝ መቀረፅ ያለበት ደንብ ሊይዘው የሚገባውን መልክ በሚከተሉት አርእስት ስር ዘርዝሮ ያቀርባል።

- አመራረት፡- በገበያ አማካይነት ለሕዝብ የሚቀርበው ጫት በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትል እንዳይሆን መቆጣጠር፣ ገበሬዎችም ብቸኛ የጫት አምራችነት ተገዥ ከመሆን ቀስ በቀስ ነፃ የሚወጡበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- አጓጓዝ፡- አሁን ያለው እና ለከፍተኛ ትራፊክ አደጋ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ያለው የጫት አጓጓዝ፣ በተለየ በጫት አጓጓዥ አሽከርካሪዎች የስነ-ምግባር እና ደንብ ላይ ባተኮረ የቁጥጥር ሥርዓት እንዲገዛ ማድረግ፣
- ንግድ፡- ጫት የሚሸጥባቸውን ቦታዎች እና ጊዜ፣ የሚሸጡ ሰዎችን እና የሚገዙ ሰዎችን የሚወስን እና የሚቆጣጠር ደንብ ማውጣት፣ የጫት ማስታወቂያዎችን ከማንኛውም ፖብሊክ ቦታ መከልከል፣ እንዲያውም ጉዳቱን ጭምር እንዲገልፁ ማድረግ፣
- አጠቃቀም፡- ጫት የሚቃምባቸውን ቦታዎች እና ጫት ከመቃም ገደብ የተደረገባቸውን የሕብረተሰብ አባሎች ለይቶ በማስቀመጥ ክልከላ ማድረግ፣
- በከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ አማካኝነት ከጫት ተያያዥ የሆኑ የሕብረተሰቡን ወጭዎች ወደ ራሱ ወደ ተገልጋዩ በማዞር አስቀድሞ ማስከፈል፡- በአሁኑ ጊዜ የጫት መቃምና ሱሰኛነት በአካባቢ ንፅሕና፣ በሰዎች

ጤና እና በመሳሰሉት የሚያደርሱት ኪሳራ የመላ ሕብረተሰቡ የጋራ ሸክም ሆኖ ይገኛል። ይህ በአንድ በኩል ከፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል መርህ ጋር የሚጣረስ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጫት የሽያጭ ዋጋ ዝቅ ብሎ ለገበያና ለቃሚው በገፍ እንዲደርስ አድርጎታል። በመሆኑም፣ የጫትን ወጭ ለጫት ተጠቃሚዎች የሚዳርግ እና የጫትን መሸጫ ዋጋ ትርጉም ባለው ደረጃ ከፍ በማድረግ የአገርውስጥ ፍጆታውን ሊቀንስ የሚችል ከፍተኛ የጫት ተጠቃሚነት ታክስ ሊጣል ይገባል።

- ስለጫት ጉዳት ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተከታታይ ዘመቻዎች በማካሄድ የባሕርይ ለውጥ ማምጣት፣- ለዚህም የተለያዩ የህዝብ ሸንጎዎችን፣ መገናኛ ብዙሃንን፣ የማኅበረሰብ ድርጅቶችን፣ የሲቪል ማሕበረሰብ ድርጅቶችን የወጣቶች ማኅበራትንና የኀይማኖት ድርጅቶችን አጋር በመድረግ መጠቀም።

ጥናቱ፣ ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት፣ የጫትን ወረርሽኝ ለመቀልበስ ከቀረቡት የመፍትሄ ሃሳቦች በተጨማሪ፣ የጫት ቁራኛ የሆኑ ዜጎችን ለመታደግ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን የምክር፣ የህክምና እና የማገገም አገልግሎት መመሪያዎች በዝርዝር አቅርቧል። እነዚህም የቀረቡባቸው ርዕሶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በአሁኑ ጊዜ በአነስተኛ ደረጃ ለሱሰኞች የሚሰጠውን የሕክምና እና ከሱሱ የማላቀቅ አገልግሎት ማስፋፋት እና ደረጃቸው ከፍ ያለ አዳዲስ ተቋሞችን ማቋቋም፣
- የአዕምሮ ጤና አገልግሎትን በየሆስፒታሎችና በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ ማካተት፣
- የአዕምሮ ጤና ሕክምናን፥ምንነቱን አውቆና ወዶ ለሚፈልግ ሰው ሚስጥራዊነትን በጠበቀ መልክ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ በማድረግ የተጠቃሚውን ሰብአዊ መብት ማስጠበቅ፣
- ለጫት ሱሰኞች የሚሰጠው የሕክምና እና የማላቀቅ አገልግሎት ሱሰኞቹ በተቋሞች በመግባት ብቻ የሚያገኙት ሳይሆን፥ በየአካባቢ ማኅበረሰባቸው እንዳሉ ሆነው የሚካሄድበትን መንገድ ጭምር መሻትና መፈተሽ፣
- ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ስፔሽያሊስት ሳይኪያትሪስቶች፣ ሳይኮሎጅስቶች የመካከለኛ ደረጃ ሶሽያል ወርከሮች በብዛት ማሰልጠን፣ እንዲሁም የአዕምሮ ሕክምና ትምህርት በማንኛውም የሕክምና ዶክተሮች ስልጠና ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣
- እስከ አሁን ድረስ የጫት ሱሰኞችን በማከምና ከሱስ በማላቀቅ በኩል አንዳንድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ የማኅበረሰብ ድርጅቶች እና መንግሥታዊ ተቋሞች ያካበቷቸውን ልምዶችና የቀሰሟቸውን ተሞክሮዎች በማካተት፣ በማራባት እና እነሱን በማሳተፍ ወደፊት የሚወሰዱ ዕርምጃዎች እንዲሰምሩ ማድረግ።

በመደምደሚያው ውስጥ፣ ጥናቱ አንድን ተጨማሪ አውራ ጉዳይ ያነሳል። ይህም የሚከተለው ነው፣ በአሁኑ ጊዜ 24 የሚሆኑ እና ቁጥራቸው እየጨመረ ያለ አገሮች የጫትን ዝውውር እና መጠቀምን ሕገ-ወጥ አድርገው ፈርጀዋል። ጥብቅ ቁጥጥርም እያደረጉ ነው።ከነዚህም ውስጥ የአለማችንን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ የሚቆጣጠሩት የሰሜን አሜሪካ፣ የአውሮፓ እና የእስያ ሃገሮች ይገኙበታል። እንደ ሳውዲ አረቢያና እስራኤል ያሉት የአካባቢያችን አገሮች ብቻ ሳይሆኑ፣ ታንዛንያ እና ኤርትራ ጭምር የነኛን ፈለግ ተከትለዋል። የዩጋንዳ ፓርላማም በጉዳዩ ላይ እየመከረ ይገኛል ተብሏል። ስለዚህ፥ ይዋል ይደር እንጅ ብዙ የሚባልለት የጫት ዋነኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭነትም ቢሆን እየመሸበት የሚሄድ መሆኑ ወለል ብሎ የሚታይ ጉዳይ ነው። በመሆኑም፣ በዚህም ረገድ ቀውስ አስወጋጅ ወይም አለዛቢ ዕርምጃዎችን አስቀድሞ ማሰብና ስትራቴጅዎችን መቀየስ ብልህነት ይሆናል።

**የራስወርቅ አድማሴ (ዶ/ር)**

ምንጭ፡-Yeraswork Admassie “ *The Khat Conundrum in Ethiopia : Socioeconomic Impact and Policy Directions*” FSS Research Monograph No.12. 2017

ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሠነድ የታተመው ከሲቪል ሶሳይቲ ድጋፍ ፕሮግራም (CSSP) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው:: ለሠነዱ ይዘት ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የተመራማሪው ሲሆን በምንም ሁኔታ የለጋሽ ድርጅቱን ወይም ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስን አቋም እንደሚያንጸባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም::

§§ አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) §§ ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

§§ ስልክ፡- 0116 29 78 88/91 §§ ፋክስ፡- 0116 29 78 89 §§ ኢሜል፡- fss@ethionet.et §§ ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org